በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

***<u>ቦታ፡</u>*** **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ግንቦት ፳፱ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

- ንስሐ ኃጢአተኛው ሰው ከእግዚአብሔር ሥልጣን በተቀበለው ካህን ፊት የኃጢአት ሥርየት ያገኝ ዘንድ ኃጢአቱን በመናዘዝ ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበት ምስጢር ነው፡፡
- ኃጢአቱን የተናዘዘውም ተነሳሒ ለተናዘዘው ኃጢአት ሥርየትን ያገኛል፡፡
- ኑዛዜ የፈጸሙትን በደል ማመን፣ መቀበልና የሠሩትን ስህተት አምኖም በትሕትና ወደ ካህኑ (መምህረ ንስሐ) ቀርቦ መናገር ሲሆን ለተናዘዝነውም ኃጢአት ሥርየት እናገኛለን፡፡
- ምስጢረ ንስሐ ጌታችን ንጹሐን ለሆኑ ሐዋርያቱ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡›› ***ማቴ 18፡18፡፡*** ባላቸው ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡
- ከትንሣኤውም በኋላ የንስሐ ሕይወትን አስመልክቶ ‹‹ኢየሱስም ዳግመኛ፡፡ ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡›› ***ዮሐ 20፡21-23፡፡*** ባለቸው ጊዜ ኃጢአትን ለማሰር ወይም ለመፍታት በመንፈስ ቅዱስ ስለተሰጣቸው ሥልጣን አረጋግጦልናል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

## *የንስሐ መታወቂያ ምልክቶች፡-*

- እውነተኛ ንስሐ አራት መታወቂያ ምልክቶች አሉት፡፡ እነርሱም፡-
    - ስላለፈው ኃጢአት የሚጸጸትና የሚቆጭ ልብ
    - ያለፍንበትን መጥፎ ሁኔታ ለማሻሻል በጽንዓት መፈለግ
    - በጌታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለን እምነት ጽኑዓን መሆንና ፍጹም ይቅር እንደሚለንም ሙሉ ተስፋ ያለን መሆን
    - በነፍስ አባት (ንስሐ አባት) ፊት ቀርቦ ኃጢአትን መናዘዝ

## *ንስሐ የምንገባበት ዕድሜ*

- ወላጆች ልጆቻቸውን ለምሳሌ ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ስለ ምስጢረ ንስሐ እንዲያውቁ ቢያደርጉ ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ ከምስጢሩ ጋር ተዋውቀው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል፡፡ ‹‹ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም::›› *ምሳ 2፡6::*

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

- ጌታችን ለንጹሐን ሐዋርያቱ ‹‹ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው::›› *ዮሐ 20፡23::* በማለት እንደነገራቸው ኃጢአትን በካህን ፊት ቀርቦ መናዘዝ እጅግ ስፈላጊ ነው፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

- የንስሐ አባታችን ኃጢአታችንን ካላወቁ እንዴት ሊያስሩና ሊፈቱ ይችላሉ? አንድ ዳኛ ስለ ጉዳዩ ምንነት ሳያውቅ ፍርድ ይሰጥ ዘንድ እንዴት ይችላል? ስለዚህም ምክንያት ምዕመናን ሁሉ የኃጢአት ሥርየት ያገኙ ዘንድ የሐዋርያትና የነርሱ ተከታዮች ሥልጣን ከተሰጣቸውና ኃጢአትንም ይቅር ይሉና ያስሩ ዘንድ ከሚችሉ ከካህናት ዘንድ ቀርበን እንናዘዝ ዘንድ አስተማሩን፡፡
- የኃጢአታችንን ሥርየት እናገኝ ዘንድ ኃጢአትን በካህን ፊት መናዘዝ አስፈላጊ ነው፡፡

## *እንደ ሰውነታችን፡-*

- የሰው ልጅ በተፈጥሮው ስለ ሐዘኑ፣ ችግሩና ጭንቀቱ የሚያነጋግረውና መልሶም የሚያረጋጋው ብሎም የሚያጽናናው ሰው ይፈልጋል፡፡
- ይልቁንም ቁልፍ ምስጢር ያለበትን ደስታችንንም ሆነ ሐዘናችንን የሚካፈለን ሰው እንፈልጋለን፤ ይህን ሊያደርግልን የሚችለው እርሱም ካህን፣ መምህር፣ እረኛችንና የምስጢራችንን ሁሉ ጠባቂ የሆነው የንስሐ አባታችን ነው፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

### *ከብሉይ ኪዳን ትምህርት አንጻር፡-*

- *መሥዋዕቱን ወደ ካህኑ ይዘው የሚቀርቡ ሁሉ እጃቸውን ለመሥዋዕት ባቀረቡት እንስሳ ራስ ላይ አድርገው ኃጢአታቸውን በካህኑና በእግዚአብሔር ፊት መናዘዛቸው አስፈላጊ ነበር፡፡ ካህኑም መሥዋዕቱን ተቀብሎ ያርደዋል፣ ስለ በደልም ፋንታ አድርጎ በመሠዊያው ላይ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ ‹‹ማንም ሰው የሚያምለውን ቃል ቢሰማ፥ ምስክር ሆኖም አንድ ነገር አይቶ እንደ ሆነ ወይም አውቆ እንደ ሆነ ባይናገር፥ ኃጢአት መሥራቱ ነውና በደሉን ይሸከማል፡፡ማናቸውም ሰው ሳይታወቀው ርኩስ ነገር ቢነካ፥ የረከሰም አውሬ በድን፥ ወይም የረከሰ ከብት በድን፥ ወይም የረከሰ የተንቀሳቀሰ እንስሳ በድን ቢሆን፥ እርሱም ርኩስ ቢሆን ነገሩ በታወቀው ጊዜ በደል ይሆንበታልወይም ርኩስነቱን ሳይውቅ ርኩስን ሰው ቢነካ፥ በማናቸውም ርኵሰት ቢረክስ፥ ነገሩ በታወቀው ጊዜ በደል ይሆንበታል፡፡ማናቸውም ሰው ሳያውቅ ክፉን ወይም መልካምን ያደርግ ዘንድ ሳያስብ በከንፈሩ ተናግሮ ቢምል ሳያስብ የማለው ስለ ማናቸውም ነገር ቢሆን በታወቀው ጊዜ ከዚህ ነገር በአንዱ በደለኛ ይሆናል፡፡ከእነዚህ ነገሮች በአንዲቱ በደለኛ ሲሆን፥ የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል፡፡ ስለ ሠራው ኃጢአት ለእግዚአብሔር የበደል መሥዋዕት ያመጣል እርሱም ከመንጋው የበግ ወይም የፍየል እንስት ለኃጢአት መሥዋዕት ይሆናል ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሰርይለታል፡፡››*

  ***<u>ዘሌዋ 5፡1-6፡፡</u>***

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

### *ከብሉይ ኪዳን ትምህርት አንጻር፡-*

- ስለዚህ ተነሳሒው በደሉን ሁሉ መናዘዝ ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ የከርሚ ልጅ የሆነው አካን ሰርቆ ሲበድል፣ የእግዚአብሔርም ቁጣ በእስራኤል ልጆች ላይ ነደደ በጋይም ሰዎች እጅ ወደቁ፡፡ ኢያሱም የከርሚ ልጅ የሆነውን አካንን አምጥቶ ‹‹ኢያሱም አካንን፦ ልጄ ሆይ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፥ ለእርሱም ተናዘዝ ያደረግኸውንም ንገረኝ አትሸሽገኝ አለው፡፡ አካንም መልሶ ኢያሱን፦ በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ እንዲህና እንዲህም አድርጌአለሁ፡፡ በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ፥ ሁለት መቶም ሰቅል ብር፥ ሚዛኑም አምሳ ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኘኋቸው፥ ወሰድኋቸውም እነሆም፥ በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል፥ ብሩም ከሁሉ በታች ነው አለው፡፡›› *ኢያ 7፡19-21፡፡*
- ንጉሥ ዳዊት በዝሙትና በመግደል ምክንያት በበደል ሲወድቅ ኅሊናው አልወቀሰውምና ‹‹እግዚአብሔርን በድያለሁ፡፡›› እንዲል የሚያበቃውን መልእክተኛውን ናታንን እግዚአብሔር ወደ ዳዊት ላከው፡፡ ‹‹ናታንም ዳዊትን፦ እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል አትሞትም፡፡›› *ካል ሳሙ 12፡13፡፡* ብሎ ነገረው፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

### *ከብሉይ ኪዳን ትምህርት አንጻር፡-*

- ናታንም ዳዊትን ‹‹ስለዚህም አቃልለኸኛልና፥ የኬጢያዊውንም የኦርዮን ሚስት ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃልና ለዘላለም ከቤትህ ሰይፍ አይርቅም፡፡... እነሆ፥ ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ ሚስቶችህንም በዓይንህ ፊት እወስዳለሁ፥ ለዘመድህም እሰጣቸዋለሁ፥ በዚህችም ፀሐይ ዓይን ፊት ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል፡፡ አንተ ይህን በስውር አድርገኸዋል እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ፡፡ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል፡፡... ›› *2ኛ ሳሙ 12፡13፡፡* ብሎ ነገረው፡፡ ‹‹ሕጻኑም ሞተ... ልጁ አቤሴሎምም ባባቱ ዳዊት ላይ አምጾ እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገበት፡፡›› *2ኛ ሳሙ 16፡2-22፡፡*
- ናታን ‹‹አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ? ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መትተሃል፥ ሚስቱንም ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃል እርሱንም በአሞን ልጆች ሰይፍ ገድለሃል፡፡ስለዚህም አቃልለኸኛልና፥ ...፡፡›› *2ኛ ሳሙ 12፡9-10፡፡* እንደተናገረው ዳዊት በቤርሳቤህ ላይ የፈጸመው ዝሙትና በኦርዮን ላይ የፈጸመው ግድያ በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመ በደል ሆኖ ተቆጥሮበታል፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

### *ከብሉይ ኪዳን ትምህርት አንጻር፦*

- ዳዊትም በነቢዩ ናታን ፊት ሲጸጸት በበደሉ ምክንያት ዘላለማዊ ሞት እንደማይሞት እንደማይጠፋም ነገር ግን ለኑዛዜው የሚገባውን ለንስሐው የተወሰኑ ቅጣቶችን እንደሚቀጣ ተነግሮታል፡፡ ጠቢቢ ሰሎሞን ‹‹ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል፡፡›› *ምሳ 28፡13፡፡* ያለውም ለዚሁ ነው፡፡

### *ከአዲስ ኪዳን ትምህርት አንጻር*

- መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ንስሐ ‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ፡፡… ን ጊዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፤ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር፡፡›› በማለት አስተምሯል፡፡ *ማቴ 3፡1-6፡፡*
- ጌታችን ለሐዋርያቱና ለተከታዮቻቸውም ‹‹እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡›› *ማቴ 18፡18፡፡* በማለት ሥልጣን ሰጥቷል፡፡ ከትንሣኤውም በኋላ ‹‹ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፡፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡›› *ዮሐ 20፡21-22፡፡* ብሏል፡፡

# <u>የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1</u>

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

### *ከአዲስ ኪዳን ትምህርት አንጻር፦*

- የጠፋው ልጅ ስለበደለው በደል ሲረዳ ወደ አባቱ ‹‹አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው፡፡›› <u>*ሉቃ 15፡21፡፡*</u> በማለት ተመልሷል፡፡
- የንስሐና የኑዛዜ ሕይወት በዘመነ ሐዋርያት እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ‹‹አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር፡፡›› <u>*የሐዋ 19፡18፡፡*</u>
- መምህራችን ቅዱስ ያዕቆብም ‹‹እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፡፡›› <u>*ያዕ 5፡16፡፡*</u> በማለት ይመክረናል፡፡
- ተነሳሒው ኃጢአቱን በካህኑ ፊት ከተናዘዘ በኋላ እግዚአብሔር ይቅር ይለውና ይህንም ኃጢአት ዳግመኛ ከመሥራት ይጠብቀው ዘንድ ካህኑ ስለተነሳሒው ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ ንስሐን ይጸልይለታል፡፡ ይህም ካህኑ ለምዕመናን እንዲናዘዝ ሳይሆን ምዕመናኑ ሁሉ ኃጢአትን ማሠር መፍታት ለሚችሉት ለካህናት ይናዘዙ ከማለቱ በተጨማሪ የተማረው ያልተማረውን እንደሚያስተምረው ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተማማሩ አለ፡፡
- ካህናትም በዕድሜና በክህነት ከእነርሱ የሚልቁ የንስሐ (የነፍስ አባቶች) አሉአቸው፡፡

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

***ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት***

***ከአዲስ ኪዳን ትምህርት አንጻር፡-***

- ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡›› *ቀዳ ዮሐ 1፡19፡፡*
- ካህኑ ባለበት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአታችንን በተሰበረ ልብ ሆነን ብንናዘዝ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለናል ከበደላችንም ፈጽሞ ያነጻናል፡፡
- ‹‹ጥምቀታችን በካህኑ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ ለልጅነታችን እንደሆነን ሁሉ ንስሐችንም በካህኑ አማካኝነት ለይቅርታ ይሆንልናል፡፡›› ቅዱስ አትናቴዎስ፡፡
- ‹‹የቤተ ክርስቲያንን አባት እንደ መንፈሳዊ አባት አክብር፤ የቆሰለ ሰው የተደበቀ ቁስሉን ለሐኪሙ ሳይደብቅ እንደሚያሳየው ሁሉ ምስጢርህንም ሳትደብቅ በግልጽ ግለጥለት፡፡›› ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘንሒሳ፡፡
- በሐዋርያት ቀኖናም ‹‹በኃጢአተኞች ሊፈረዱና ኃጢአተኞችንም ሊቀጡ የማሰርን እንዲሁም ለተነሳሕያን ኃጢአታቸውን ይቅር ለሉ የመፍታትን የሕይወት ሥልጣን ከእግዚአብሔር ተቀብለዋልና መንፈሳውያን አባቶችን አክብራቸው፡፡›› ተብሎ ተጽፎልናል፡፡

# <u>የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1</u>

## *ኃጢአትን ለካህን የመናዘዝ አስፈላጊነት*

### *ከአዲስ ኪዳን ትምህርት አንጻር፡-*

- ‹‹አልዓዛርን ከሞት ካነሳው በኋላ ሐዋርያቱ መግነዙን እንዲፈቱ አዘዛቸው፡፡›› ቅዱስ አውግስጢኖስ፡፡ ጌታችን ኃጢአትን ይቅር ይሉ - ይፈቱ ዘንድ ለሐዋርያቱና ለተከታዮቻቸው ሥልጣን እንደሰጠ ያስተምረን ዘንድ ይህን አደረገ እንጂ ሕይወትን የሰጠ የመግነዙን ልብስ መፍታት የማይቻለው ሆኖ አይደለም፡፡
- ካህናት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በፍጹም ንስሐ ለገቡት እንጂ ለማይገባቸው እንዲያቀብሉ አይገባም - በቸልተኝነታቸው በእግዚአብሔር ፊት ይጠየቁበታልና፡፡ ቀሳውስትን በሚሾሙበት ጊዜ በተሠራው ሥርዓት ጳጳሱ ወይም ሊቀ ጳጳሱ እንዲህ በማለት ያነብባል፡፡ ‹‹ይህችን ሀብት ኪሩብ የሕይወትን ዛፍ እንዲመለከቱ አድርገህ ተመልከታት፤ ይህንም ምስጢር አስመልክቶ ከውድቀት፣ ከድቀት ከቸልተኝነት ራስህን ጠብቅ - ቁርባኑንም ለሚገባቸው፣ መልካም ሥነ ምግባርን ከሃይማኖት ጋር አስተባብረው በንጹሕ ልብ ከሚሆኑት በቀር አታቀብል፡፡ ኃጢአተኛውንም እንዳይጠፉ ጠብቀው፡ ቢጠፉ ትጠየቃለህና፡፡››
- ካህኑ ልቦናው ንጹሕ የሆነውን ካልሆነው የሚለየው ለቅዱስ ቁርባን የሚገባ መሆን አለመሆኑን የሚያውቀው በካህኑ ፊት ቀርቦ በመናዘዙ አይደለምን?

# የንስሐ ሕይወት - ክፍል 1

*ከአዲስ ኪዳን ትምህርት አንጻር፦*

- ጌታችን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለሚያውቁትና ለሚገባቸው እንደሰጠ ንስሐ የማይገባውን ኃጢአቱንም የማይናዘዘውን ከቅዱስ ቁርባን እንዳይሳተፍ ይከለክል ዘንድ ካህኑ ሥልጣን አለው፤ የአስቆሮቱ ይሁዳ በክፋቱ የተነሳ ከቅዱስ ቁርባን ይኸው ተደርጎበታልና፡፡
- ኃጢአትን ለካህን ተናዝዞ ይቅርታ እንዳገኘን መስማት የነፍስ ደስታ ነው! ኃጢአታችንን ለካህኑ በተሰጠው ሥልጣን ይቅር ተብለናልና፡፡
- ኃጢአትን በካህኑ ፊት የሚናዘዝ ሰው ጥበብን ከተሞላው ልምዱም ካለው ከካህኑ ምክሩን ያገኛልና ምክሩን በመታዘዝና በቅንነት ቢፈጽመው ከኃጢአት ጋር በሚያደርገው ትግል አሸናፊና ተጠቃሚ ይሆናል፡፡
- በኑዛዜ ጊዜ የሚኖረው ሐፍረት በኃጢአት ለወደቀችው ነፍስ ቅጣትዋ ሲሆን፤ ካህኑም የሚሰጠን ቀኖናም (ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት፣ ስግደት) ከነፍስ ጋር ተባብራ በኃጢአት ለተገኘች ለሥጋ የሚሰጥ ቅጣት ነው፡፡
- በርካታ ሰዎች በማፈራቸው የተነሳ ፈርተው በካህናት ፊት ከመናዘዝ ርቀው ለእግዚአብሔር ቀጥታ እናዘዛለሁ በማለት ከተጻፈላቸው ውጪ የሆነ መንገድ ዘርግተው ይሸሻሉ፡፡
- ነገር ግን ተነሳሕያን በምንናገርበት ጊዜ የሚሰማን ሐፍረት በእግዚአብሔር ፊት የሠራነውን ኃጢአት አሳፋሪነት የምንረዳበት እጅግ አትራፊ ጎዳና እንደሆነ እንወቅ፡፡ በካህናት ፊት ከመናዘዝ የምንሸሸው በትዕቢትና በትምክህት የተነሳ ነው፤ ትዕቢተኛ በካህኑ ፊት ትሑት ሆኖ ይገኝ ዘንድ አይቻለውምና፡፡

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org